# ጋዜጣዊ መግለጫ



አሜሪካ ኤምባሲ

አዲስ አበባ

2013/25

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ

ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

---

## የአሜሪካ መንግሥት በትምሕርት ቤቶች የወተት ቀን በዓልን ማክበር ጀመረ

***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ኅዳር 12 ቀን 2006 ዓ.ም.፡-*** የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲው ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ በኩል “የወተት ቀን በትምሕርት ቤት” በሚል ርዕስ በ14 ትምሕርት ቤቶች ከሚያካሂዳቸው ዝግጅቶች የመጀመሪያውን በዛሬው ዕለት በአማራ ክልል በሚገኘው ውሻውሺኝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምሕርት ቤት ጀመረ፡፡ የነዚህ ዝግጅቶች ዓላማ ዕድሜያቸው ለትምሕርት የደረሰ ልጆች፣ ወላጆች እና መምህራን ስለወተት ያላቸውን እውቀትና ግንዛቤ ማሳደግ ነው፡፡

ወተት ለጤናማ የአካል ዕድገትና መዳበር በሚሰጠው ስነ-ምግባዊ ጠቀሜታ ላይ ትኩረት የሚያደርገው የዚህ ዘመቻ ዋና መልዕክትም፤ የፈላ ወይም ፓስቸራይዝድ የሆነ ወተት ጤናማ እንደሆነ እና ለዚህም ወተቱን ማፍላት ብቻ በቂ እንደሆነ ማሳወቅ ነው፡፡በ14ቱ ዝግጅቶች የሚሳተፉ ትምሕርት ቤቶች በየአካባቢው ቋንቋ የተዘጋጁ መረጃዎች፣ ካኒቴራዎች እና የመምህራን መምሪያዎች እንዲደርሷቸው ይደረጋል፡፡ እነዚህ ማስተማሪያዎች የፈላ ወይም ፓስቸራይዝድ የሆነ ወተት የመጠጣትን ጥቅም በሚያዝናና እና ከወጣቶች ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲያቀርቡ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

የ ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ኢትዮጵያ ሚሽን ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር፤ “የወተት ቀን በትምሕርት ቤት በዓል ሕጻናትም ሆኑ አዋቂዎች ወተት የመጠጣትን ጥቅም እና አስፈላጊነት እንዲረዱ ያግዛል፡፡ በዚህ ዘመቻ ሰዎች ስለወተት እና ለጤናማ ዕድገት ስለሚኖረው ጠቀሜታ ይበልጥ እንደሚረዱ ተስፋ እናደርጋለን፡፡” ብለዋል፡፡የዓለም የወተት ቀን በብዙ የዓለም አገራት በወርሃ መስከረም ይከበራል፡፡ በበዓሉ ላይ ወተት እና የወተት ተዋጽኦዎች ለሕጻናት እና ለአዋቂዎች የሚሰጡትን ስነ-ምግባዊ ጠቀሜታ የሚያጎሉ አዝናኝ ዝግጅቶች ይቀርባሉ፡፡ እ.ኤ.አ. ከመስከረም 2000 ጀምሮ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ40 የሚበልጡ አገራት የወተት ቀንን በየዓመቱ ያከብራሉ፡፡ በዚህ ዓመትም ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ዝግጅቶቹን በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ እና ትግራይ ክልሎች በሚገኙ 14 ትምሕርት ቤቶች ለማቅረብ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ዘመቻ በዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የግብርና ዕድገት መርሃግብር የእንስሳት ገበያ ልማት ፕሮጀክትን የሚያጠናክር ሲሆን፤ ይህ ደግሞ በተራው የአሜሪካውን ፕሬዚደንት ፊድ ዘ ፊውቸር መርሃግብር ያጠናክራል፡፡ ቀጣዩ የኢትዮጵያውያን ትውልድ በአገር ውስጥ የሚመረቱ የወተት ውጤቶችን በይበልጥ መጠቀሙ የትውልዱን አመጋገብ ከማሻሻል ባለፈ የአገሪቱንም የምጣኔ ኃብት ዕድገት ወደ ላቀ ደረጃ ያደርሳል፡፡

###